የሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 15 እና 16

1. በምዕራፍ 15 ላይ ያለው የጠፋው ልጅ ታሪክ ላይ የልጆቹ ምሳሌነት ለየቱ ነው?
ሀ) ትልቁ ልጅ የጸሐፍት ፈሪሳውያን፣ ትንሹ ልጅ የኃጥአን መጸብሓን
ለ) ትልቁ ልጅ የባሕታውያን፣ ትንሹ ልጅ የሰብአ ዓለም (በዓለም የሚኖሩ ሰዎች)
ሐ) ትልቁ ልጅ የመላእክት ትንሹ ልጅ የደቂቀ አዳም (የሰው ልጆች)
መ) ሁሉም መልስ ናቸው

2. ከሚከተሉት ታሪኮች ውስጥ በሉቃስ ወንጌል ላይ ብቻ ተጽፎ የሚገኘው የትኛው ነው?
ሀ) የጠፋው በግ ለ) የጠፋው ልጅ ሐ) ስለንጉሥና አገልጋዮቹ መ) ሀ እና ለ

3. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ “ለሁለት ጌቶች መገዛት የሚችል አገልጋይ የለም” ሲል ጌቶች ያለው እነማንን ነው?
ሀ) እግዚአብሔር እና የሚያመልኳቸው ጣዖቶች

ለ) ጣዖት እና ገንዘብ
ሐ) እግዚአብሔር እና ገንዘብ
መ) ሁሉም መልስ ናቸው

4. በምዕራፍ 16 ላይ ያለው ታሪክ ላይ መጋቢው ጌታው ሊያባርረው እንደሆነ ሲያውቅ ምን አደረገ?
ሀ) የጌታውን ባለዕዳዎች ጠርቶ ዕዳቸውን ቀነሰላቸው
ለ) ጌታውን እንዲምረው ሄዶ ለመነው
ሐ) ከጌታው ገንዘብ ላይ ለራሱ የሚሆን ሰርቆ ወሰደ
መ) ሀ እና ለ

5. በምዕራፍ 16 ላይ ያለው ታሪክ ላይ ያለው የሹሙ ምሳሌነት ለየቱ ነው?
ሀ) ንስሐን የማያስተምሩ፣ ነገር ግን በጽኑ በታመሙ ጊዜ የነፍስ ልጃቸውን ጠርተው ቀኖና ሰጥተው “እኔ እኩሉን እጾምልሃለሁ” ብለው ቀኖናውን ያቀለሉለት መምሕረ ንስሐ
ለ) ሥልጣኔን ከመቀማቴ በፊት የምችለውን ያክል ዘርፌ ለራሴ ልውሰድ የሚል ባለሥልጣን
ሐ) ጌታ ነፍሴን ከስጋዬ ሳይለያት በፊት ለነዳያን መጽውቼ ለነፍሴ ልትረፍ ብሎ የሚያስብ አንድ ባለጸጋ

መ) ሀ እና ሐ

6. በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 15 ላይ ታናሹ ልጅ ወደ አባቱ ቤት በተመለሰ ጊዜ ታላቁ ልጅ በየት ነበር?
ሀ) በኋደኛው ቤት ለ) በእርሻ ሐ) በምኩራብ
መ) በመዝናኛ ቦታ

7. ነቄ ስንት ወንድሞች ነበሩት?
ሀ) 10 ለ) 5 ሐ) 2 መ) መልሱ የለም

8. ነቄ አብርሃም አልዓዛርን ወደ ዘመዶቹ እንዲልከው የጠየቀበት ምክንያት ምን ነበር?
ሀ) የሚያስተምራቸው ስላልነበረ
ለ) ከሙታን አንዱ ወደ እነርሱ ሄዶ ካልነገራቸው ንስሐ አይገቡም ብሎ
ሐ) እሱ ወዳለበት የስቃይ ቦታ እንዳይመጡ
መ) ለ እና ሐ

9. በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 16 ላይ አብርሃም "...

በእኛና በእናንተ መካከል ታላቅ ገደል አለ" ሲል ገደል የተባለው ምንድነው?
ሀ) ጭካኔ ለ) የእግዚአብሔር ፍትሕ ሐ) ሰማይ መ) ይህች ዓለም

10. በአልዓዛርና በነቄ ታሪክ ውስጥ የነቄ መጨረሻ ምን ሆነ?
ሀ) በሲዖል ሳለ አብርሃም አዝኖ አልዓዛርን ውሃ እንዲያጠጣው ላከለት
ለ) በሲዖል ሳለ ስለተጸጸተ ነፍሱ ተምራ ወደ ገነት ሄደች
ሐ) ለዘመዶቹ እንዲያስተምር ተላከ
መ) መልሱ የለም

11. ከአልአዛርና ከነቄ ታሪክ ምን እንማራለን?
ሀ) ቅዱሳን በአጸደ ነፍስ እንደሚያማልዱ
ለ) በምድር ላይ በጎ ምግባር ባይኖረን እንኳ ድኑነን ሆነን በችግር ከኖርን እግዚአብሔር ከመንግስቱ እንደማያሳጣን
ሐ) ለተቸገሩ ሰዎች በጎነትን ብናደርግ እግዚአብሔር ብድራታችንን እንደሚከፍለን
መ) ሀ ና ሐ

ሠ)ሁሉም

12. በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 15 ላይ ባለው የጠፋው በግ ምሳሌ ላይ የጠፋውን በግ ሲያገኘው ምን አደረገው?
ሀ)እየመታ እና እየገረፈ ከዘጠና ዘጠኙ ጋር ጨመረው
ለ)ሸጠው
ሐ)አርዶ በላው
መ) በትከሻው ላይ ተሸከመው

13. በቅ. ሉቃስ ወንጌል ላይ በተጠቀሰው መሰረት በሰማያት ፍጹም ደስታ ሚደረገው መቼ ነው?
ሀ)ኅጢአተኛ ንስሐ ሲገባ
ለ)በጎች ሲጠፉ
ሐ) ጻድቃን ኑሮአቸውን ሲኖሩ
መ)ሁሉም

14. በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 15 ላይ ያለው የድሪም ምሳሌ ላይ ስንት ድሪም እንደጠፋ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አስተማረ?
ሀ)2 ለ)1 ሐ)9 መ)10

15. ድሪም ምንድን ነው?
ሀ)ሳንቲም ለ)የአንገት ሀብል ሐ)የእጅ አምባር መ)ለ እና ሐ

16. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 15 ላይ ከሰጣቸው ሶስት ምሳሌዎች ውስጥ አውቆ በፈቃዱ ሊጠፋ የሚችለው የቱ ነው?
ሀ)የጠፋው በግ
ለ)የጠፋው ድሪም
ሐ)የጠፋው ልጅ
መ)ሀ እና ሐ

17. "ከእናንተ ወገን 100 በጎች ያሉት ቢኖር ከመቶው አንዱ ቢጠፋበት....." ብሎ ጌታችን ባስተማረው መሰረት ትክክል ያልሆነውን ምረጡ
ሀ ) ከ 100 ው ነገደ መላእክት ሰይጣን ቢጎል አዳም በርሱ ተተክቷል
ለ) ሰይጣን ከ 100 ው ነገደ መላእክት ቢጠፋ ክርስቶስ በቸርነቱ እርሱንም በዛው ሊመልሰው መቷል
ሐ) አዳም ከ 100 ው ነገድ ቢጠፋ ክርስቶስ በቸርነቱ

99ኙን ነገደ መላእክት ትቶ እርሱን ሊመልሰው መቷል
መ)መልሱ የለም

18. በሉቃስ ወንጌል ላይ ወርቅ በተሞላ አሮጌ ሳጥን እና ጠጠር የተሞላ ባጌጠ ሳጥን የተመሰሉት እነማን ናቸው?
ሀ) ባሕታውያን እና ኀጥአን
ለ) ሰዎች እና መላእክት
ሐ) ካሕናትና ዲያቆናት
መ)ሁሉም

19. በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 16 ላይ ባለጸጋው በሞተ ጊዜ ከማን ጋር ተነጋገረ?
ሀ)ከእግዚአብሔር ለ)ከሙሴ ሐ)ከአልዓዛር መ)ከአብርሃም

20. በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 16 ላይ ባለጸጋው በቅደም ተከተል ለማን ለማን ለመነ?
ሀ)ለራሱ፣ ለወንድሞቹ
ለ)ለሀገሩ፣ ለራሱ፣ ለሚስቱ
ሐ)ለቤተሰቡ፣ ለሀገሩ

መ)ለማንም

21. በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 15 የመቶው በግ ባለቤት አንዷ በግ ስትጠፋ ዘጠና ዘጠኙን በየት ትቷቸው አንዷን ሊፈልግ ሄደ?
ሀ)በተራራ ለ)በቤቱ ሐ)ከእርያዎች ጋር
መ)በምድረ በዳ